# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 143 የካቲት 3 2003 ገጽ 1


**የትግራዩ ገገር ጉጅሌ የኢትዮጵያን ህዝብ ለመከፋፈል ከሚጠቀምባቸው መሣሪያች አንዱ የእምነት ተቋማት ናቸው፤ በጅማ፣ በሃረር፣ በአዲስ አበባ፣ በጎንደርና በደሴ የደረሱ ሃይማኖትን መሠረት ያደረጉ ግጭቶች ሁሉ የወያኔ ከፊል ስውር፣ ከፊል ገሃድ እጅ እንዳለባቸው ጥርጥር የለውም። ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ አላስፈላጊ የሃይማኖት ክርክሮች ቁመው የመለስ ዜናዊን አገዛዝ ለማስወገድ በኅብረት እንነሳ ይላል።**

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## ሙባረክ ከስልጣናቸውን ለቀቁ፣ የግብጽ ህዝብ በተገኘው ድል ደስታውን እየገለጸ ነው

ከትናንት በስቲያ የሙባረክን ከስልጣን የመውረድ ዜና ለመስማት የካይሮዉን ተሕሪር አደባባይ አጨናንቆት የዋለው የግብፅ ሕዝብ በፕሬዘደንት ሙባረክን ንግግር ከመቼውም ጊዜ በላይ ቁጣና እልህን ማሳየት መጀመሩ የሚታወስ ሲሆን የሙባረክን ንግግር ተከትሎ የአሜሪካው ፕሬዘደንት ባራክ ኦባማ ሙባረክ የወሰዱት ርምጃ በቂ አይደለም የግብጽ ህዝብ ጥያቄ እንዲመለስና በሃገሪቱም የዴሞክራሲያዊ ስርአት ምስረታ እውን እንዲሆን ከተፈለገ ሙባረክ ለግብጻዊያን ጥያቄ መልስ ሊሆን የሚችል ስር ነቀል ርምጃ ሊወስዱ ይገባቸዋል ማለታቸው አይዘነጋም::

የግብጽ ህዝብ አዲስ ቁጣና እልህ ያገረሸው ፕሬዘደንት ሆሲኒ ሙባረክ ከስልጣን የመውረዳቸውን ዜና ያበስራሉ ሲባል እስከ መስከረም ወር ድረስ አሁንም በስልጣን ላይ እንደሚቆዩኡና ለተጨማሪ ጊዜ በፕሬዘዳንትነት እንደማይወዳደሩ መግለጻቸውን ተከትሎ ነው::

ይሁን እንጂ የፕሬዝዳት ሆስኒ ሙባራክ አገዛዝ፥ ሙስና፥ ሥራ አጥነት፥የኑሮ ዉድነት ያስመረረዉ የግብፅ ሕዝብ የአደባባይ ሠልፍ እና አመፅ በከፍተኛ ሁኔታ በትናንትናው እለት ከሃያ ሚሊዮን የሚበልጡ ግብጻዊያን በሁሉም የሃገሪቱ ክፍሎች እየተሰሳተፉ ባለበት ወቅት ሆስኒ ሙባረክ ቤተመንግሥታቸውን ወደኋላ ትተው ወደ ቀይ ባህር ዳርቻ ለመሸሽ ተገደዋል።

በካይሮዉ ተሕሪር ወይም የነፃነት-አደባባይ ሰልፍ አስራ ሰምንተኛ ቀኑን በያዘበት በትናንትናው እለት ከቅርብ ቀናት ቀደም ብሎ ያልተሳተፉ ገና በእድሜያቸው ለጋ የሆኑ በሺህ የሚቆጠሩ ወጣቶች ሰልፉን የተቀላቀሉ ሲሁን ከወንዶቹ ይልቅ የሴቶቹ ጥንካሬ ደግሞ አስገራሚ እንደነበር የተለያዩ የዜና አውታሮች ዘግበዋል:: በካይሮው አደባባይ የህጻናት የወጣቶች የሴቶችና የሽማግሌዎች ድምጽ በአንድነት «ሙባረክ መሔድ አለበት እኛ አንሔድም።» በማለት ሲያስተጋባ እንደነበር አይዘነጋም:: (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ የአስቸኳይ የምግብ እርዳታ እፈልጋለሁ አለ

አምባገነኑና ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ በሁለት አሃዝ አገሪቱን በልማት አሳድጊያለሁ፣ በያዝሁት የትራንስፎርሜሽን እቅዴ መሰረት ምንም አይነት ተረጂ አይኖረኝም ባለ አንድ አመት እንኳአን ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ለሁለት ነጥብ ስምንት ሚሊየን ሕዝብ አስቸኳይ የምግብ እርዳታ ያስፈልገኛል ሲል የተለመደውን ልመና ለለጋሽ አገሮች ማቅረቡ ታወቀ። ይህን የልመና ጥያቄ ተከትሎ የወያኔው አገዛዝ ባለስልጣናት የእርዳታ ጠባቂው ቁጥር ባለፈው ዓመት ከነበረው በብዙ እጥፍ ወርዶአል፤ አርባ ከመቶ የሚሆነው የምግብ እጥረት የተከሰተው በሰላም እጦት ተቸግሮ በሚገኘውና የተበታተነ የሕዝብ አሠፋፈር ባለበት በኢትዮጵያ ሶማሌ ክልል ነው ማለቱም ታውቆአል፡፡

ይህንን ዜና አስመልክቶ አስተያየት እንዲሰጡን ዘጋቢያችን ከአዲስ አበባ ያናገራቸው አንድ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ እንደገለጹት የወያኔው አገዛዝ ባለስልጣናት በቢሊየኖች የሚቆጠር ዶላር በውጪ ሃገር ባንኮች የግል አካውንታቸው እያጠራቀሙ ባለበት ባሁኑ ወቅት አሁንም በረሃብተኛ ኢትዮጵያዊያን ስም የዓለምን ህዝብ ገንዘብ ርዳታ አድርጉልኝ ብሎ መለመን ውጤቱ ምን ሊሆን እንደሚችል መገመት አያዳግትም ብለዋል:: አስተያየት ሰጪው አክለውም፣ ኢትዮጵያ ዛሬ በጣም ጥቂት የሆኑ የቡድን አባላት ብቻ እንደፈለጉ የሚንፈላሰሱባት እጂግ በርካታውና አብዛኛው የኢትዮጵያ ህዝብ ግን የዕለት ጉርሱን መሸፈን ተስኖት ለሚያስተዳድራቸው ቤተሰቦቹ ምግብ በፈረቃ ለማቃመስ ተገዶአል ብለዋል:: በመጨረሻም ከንዲህ አይነቱ አገዛዝ መላቀቂያ መንገዳችን አንድ ነው፣ እሱም የሚያደራጀንና የሚመራን ብናገኝ እንደቱኒዚያ ህዝብ ሆ ብለን ተነስተን አገዛዙን ከስሩ መንግለን መጣል ነው ብቻ ነው በማለት አስተያየታቸውን አጠቃለዋል::

ሂዩማን ራይትስ ዋች የተሰኘው ዓለም አቀፍ የሰባዊ መብቶጭ ጥበቃ ተቋአም፣ የውያኔው አገዛዝ ከዓለም አቀፉ ህብረተሰብ የሚያገኘውን ርዳታ ለፖለቲካ ፍጆታ እያዋለ ነው በማለት የከሰሰ መሆኑ አይዘነጋም::

## መለስ ዜናዊ በሙኒክ ጀርመን ከፍተኛ የሆነ ተቃውሞ ገጠመው

እንደፈረንጆች አቆጣጠር ከፌብሪዋሪ 4 እስከ 6 በሙኒክ ከተማ በተደረገው የጸጥታ |ሴኩሪቲ| ስብሰባ ላይ ለመገኘት በጀርመን የልማት ትብብር ሚንስቴር ተጋብዞ የነበረው ዘረኛውና አምባገነኑ መለስ ዜናዊ በጀርመንና አካባቢው በሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ከፍተኛ የሆነ ተቃውሞ እንደገጠመው የግንቦት 7 ድምጽ ተባባሪ ዘጋቢ ከሙኒክ ከተማ በላከልን ዜና ለማወቅ ተችሎአል። ቁጥራቸው ወደ 3 ሺ የሚገመት ኢትዮጵያዊያን በነቂስ ወጥተው ባሰሙት የተቃውሞ ሠልፍ፤ መለስ ዜናዊ ነፍሰ ገዳይ ነው፤ መለስ ዜናዊ አምባገነንና በዜጎቹ ላይ ሰቆቃ የሚፈጽም ነው፤ መለስ ዜናዊ ሌባ ነው ፤ በጋምቤላ፤ በኦጋዴን፤ በኦሮሚያና ሌሎች ቦታዎች ለፈጸመው ዘር ማጥፋት ወንጀል ለፍርድ ይቅረብ ወዘተ የሚሉ መፈክሮች ሲስተጋቡ መዋላቸው ተዘግቦአል።

የኢትዮጵያ ሳታላይት ቴሌቪዥን ኢሳት በኢትዮጵያዊያኑ የተደረገውን ተቃውሞ በቀጥታ ከስፍራው ለኢትዮጵያዊያን አድማጮቹ ያስተላለፈ ሲሆን በየግላቸው ተቃውሞ ሰልፉን አስተባብረው የወጡ የኦጋዴን እና የኦሮሚያ ነጻነት አቀንቃኞች (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ህዝባዊ አመጽ እንደሚነሳበት ስጋት የገባው የመለስ አገዛዝ ከፍተኛ አጣብቂኝ ውስጥ እንዳለ ታወቀ

በሌሎች መሰረታዊ የምግብ ፍጆታ እቃዎች ላይ የሚጨመረው ዋጋ ንረት ከዕለት ወደ ዕለት ህዝባችንን የኑሮ ውድነቱን መቋቋም ከማይቻልበት ደረጃ ላይ ሲያደርሰው "የኢኮኖሚያችን ማደግን አመልካች ነው" እያለ ሲያላግጥ የኖረው ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ በቱንዚያ ፈንድቶ አምባገነኖች ያሉበትን አገራት እያዳረሰ ያለውን ህዝባዊ ቁጣ በመፍራት ጊዜያዊ የሽንገላ እርምጃ መውሰዱን እንደቀጠለ መሆኑን የውስጥ አዋቂ ምንጮች ለግንቦት 7 ዘጋቢ ገለጹ። እንደዘጋቢያችን ምንጮች ቀደም ሲል በአለም አቀፍ የነዳጅ ዋጋ መለዋወጥ ሽፋን በሰበብ አስባቡ ይጨምር የነበረው የነዳጅ ዋጋ ላለፉት ወራት እንዳይጨምር ከፍተኛ ቁጥጥር እየተደረገ እንደሆነና በዚህም ምክንያት የነዳጅ ዕጥረት በአብዛኛው የነዳጅ ማደያዎች በመፈጠሩ ነዳጅ ለመሙላት ታይቶ የማይታወቅ ወረፋ በየቦታው እየታየ መሆኑ ታውቆአል።

ዘጋቢያችን ስለሰሞኑ የነዳጅ ወረፋ መራዘም ያነጋገራቸው የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች በሰጡት አስተያየት በቱኒዚያ ተቀጣጥሎ እንደሰደድ እሳት በተለያዩ የአፍሪቃ ሃገራት እየተዛመተ ያለው የህዝብ አመጽ እንቅልፍ እንደነሳውና ይህም በመሆኑ በቁዋፍ ላይ ባለው ህዝብ ላይ የነዳጅ ዋጋ ጭማሪ ቢደረግ አመጹ ድንገት ሊፈነዳ ይችላል ከሚል ፍራቻ መሆኑን ገልጸዋል:: ይሁን እንጂ ቀን መቁጠር ካልሆነ በስተቀር የኢትዮጵያዊያን ብሶት አንድ ቀን መፈንዳቱ አይቀሬ እንደሆነ አስተያየት ሰጪዎቹ አክለው ገልጸዋል::

ከዚሁ ጋር ተያይዞ የአዲስ አበባው ዘጋቢያችን ባስተላለፈልን ሪፖርት የአዲስ አበባ ከተማና በሌሎች ከተሞች የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን ዘረኛው አገዛዝ የማሙኢያ ምርጫ አካሂዱ በማለት ጥያቄ ቢያቀርብም ለጥሪው ማንም ጆሮ ሳይሰጠው እንደቀረ ለማወቅ ተችሎአሎ:: በዚህም ምክንያት የአምባገነኑ ወያኔ ካድሬዎች በየቦታው እየተዘዋወሩ ህብረተሰቡን ማስፈራራት መቀጠላቸውንም ዘጋቢያችን ከስፍራው ባስተላለፈልን ሪፖርት ገልጹአል:: (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## የጨፌ ሮቢ ወረዳ አንድ አርሶ አደር የዘረኛውን አገዛዥ ታጣቂዎች መግደላቸው ታወቀ

የቦርከና ወንዝ የሚያመጣውን ደለል ተጠቅመው ጤፍና ሌሎች ሰብሎች በማምረት እየተገለገሉበት የነበረን ቦታ ቦታው የከብቶች ግጦሽ ቦታ ነው፣ በመሆኑም በማሳ ላይ የሚገኘውን ሰብል በከብቶች እንዲበላ ይሁን በማለት የወረዳው ሆድ አደር ባለስልጣናት በመወሰናቸው ሰው የሚበላውን አጥቶ እየተቸገረ ባለበት ወቅት እንዴት ሰብልን ከብት እንዲበላው ትወስናላችሁ በማለት የተበሳጩ አርሶ አደር አንድ ፖሊስ ገድለው በርካቶችን ማቁሰላቸውን ኢሳት የዜና ምንጮቹን በመጥቀስ ዘግቡአል::

እንደ ኢሳት ዘገባ አርሶ አደሩ በወቅቱ ከፖሊሶች ጋር በተደረገው የተኩስ ልውውጥ መሞታቸው የታወቀ ሲሆን ምናልባት የሙዋች አርሶ አደር ልጆች ሳይሆኑ እንዳልቀሩ የተገመቱ ሌሎች አርሶ አደሮች ጨፌ ሮባ ወረዳ ፖሊስ ጣቢያ ድረስ በመሄድ የወረዳውን ፖሊስ አዛዥ ገድለው መሰወራቸውን ዘግቡዋል::

ከዚሁ ጋር በተያያዘ የአካባቢው አርሶ አደሮች በሰጡት አስተያየት ለሆዳቸው ያደሩ የወረዳ ባለስልጣናት ውሳኔዎችን የሚወስዱት በራሳቸው ስልጣን ተጠቅመውና ከወያኔው አገዛዝም በቀጥታ በሚሰጣቸው መመሪያ በመሆኑ የህብረተሰቡን ፍላጎት በፍጹም አያዳምጡም፣ ቢያዳምጡ ኖሮ ይህ ሁሉ ደም መፋሰስ ባልደረሰ ነበር በማለት መናገራቸው ታውቁአል::

ኢትዮጵያዊያን ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ እያደረሰባቸው ያለው በደልና ግፍ እጂግ እየበዛ በመሄዱና አብዛኛው የብረተሰብ ክፍል ትእግስቱ በመሙዋጠጡ በአገዛዙ ባለስልጣናት ላይ የተናጠልና የቡድን ርምጃ በተለያዩ የሃገሪቱ ክፍሎች እየተወሰደ መሆኑን መዘገባችን አይዘነጋም::

## የወያኔ ካድሬዎች ከፌዴራል ፖሊሶች ጋር በመሆን "የሥልጠና፣ የሥራ ቦታ እና የብድር አገልግሎት መስጫ" ፎርም ማስሞላት ጀመሩ

ሰሞኑን በቱኒሲያው ተጀምሮ ለሎች አምባገነኖች የሚኖሩባቸውን ሀገራት እያናወጸ ያለው ህዝባዊ አመጽ ያስደነገጣቸው የወያኔ ጎጠኛ መሪዎች ራሳቸውን ለመከላከል ሲራወጡ መሰንበታቸው ለዚህም ወታደሮቻቸውን በተጠንቀቅ እንዲቆም ትእዛዝ ከመስጠት ጀምሮ አድማ በታኝ ፖሊሶችንና ካድሬዎቻቸውን አጫጭር ሲልጠናዎችንና ማስጠንቀቂያዎችን ሲሰጡ እንደሰነበቱ መዘገባችን ይታወሳል።

ይህንኑ ተከትሎ ከሰኞ ጥር 23 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ የወያኔ ካድሬዎች በፌዴራል ፖሊሶች በመታጀብ በየቀበሌው አደገኛ ቦዘኔ በማለት ይፈርጁዋቸው የነበሩትን ወጣቶች እና ሴቶችን "የሥልጠና፣ የሥራ ቦታ እና የብድር አገልግሎት መስጫ" የሚል ፎርም እየዞረ ማስሞላት መጀመራቸውን ዘጋቢያችን ከስፍራው ከላከልን ሪፖርት ለማወቅ ተችሎአል፡፡ እንደ ሪፖርተራችን ዘጋባ ምዝገባው የተካሄደው ባለፈው ሳምንት ሴቶችንና ወጣቶችን በየከተማው ክልል በማሰባሰብ በ5ቱ አመት የእደገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ለናንተ የኑሮ ዋስትናና እድገት እንሰራለን፡ እናንተ ግን አትቃወሙን የሚል የፍርሀት ማስጠንቀቂያ አዘል ንግግር በባዶ ተስፋ ከታዘለ የማዘናጊያ ቅስቀሳቸ ጋር በየቦታው በሰፊው ካካሄዱ በኋላ እንደሆነ ታውቆአል። ማስጠንቀቂያ አዘል የውሼት ተስፋ ከተገባላቸው ወጣቶች አንዳንዶቹን ያናገረው ዘጋቢያችን ፤ ወያኔ እስከ ዛሬ በገባቸው ቃልከዳኖች የህብረተሰቡን በተለይም የወጣቱን ኑሮ ለማሻሻል እንዳልተሳካለት አንደሚያውቁ ገልጸው፤ በብልሹ አስተዳደር ምክንያት የተንሰራፋው ድህነት ያስከተለውን ቀውስ የተወሰነ የህብረተሰብ ክፍል በመደለል ለመወጣት መሞከር የተለመደ የወያኔ ከፋፍሎ የመግዛት ሥልት ነው በማለት በስብሰባው ላይ የተገባላቸው ባዶ ተስፋ ካብጠለጠሉ ቦኋላ ለነጻነታቸው ከመደራጀት እና በዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ላይ ሆ ብለው ከመነሳት ሊያግዳቸው እንደማይችል ተናግረዋል። በሥልጣን ዘመናቸው በሙስናና የህዝቡን ሃብት በመዝረፍ የከበሩ አምባገነኖች ላይ በሰሜን አፍሪካ (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## የነፃነት ትግል የጋራ፤ ሃይማኖት የግል ነው!

“አገር የጋራ ነው፤ ሃይማኖት ግን የግል ነው” የሚለው መርህ በአገራችን ከፍተኛ ትርጉም ያለውና ማኅበራዊ ተቀባይነትንም ያገኘ የቆየ ብሂል ነው። ሙስሊምና ክርስቲያን ዜጎች ተከባብረው እንዲኖሩ፤ ተባብረው ነፃነታቸውን እንዲያስከብሩ ይህ ብሂል ያበረከተው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው። በዚህም ምክንያት ኢትዮጵያ አገራችን የክርስትናና የእስልምና እምነቶች ተቻችለው መኖር እንደሚችሉ ለማሳየት የቻለች አገር ናት።

ህዝብ ሰብዓዊ ክብሩን ለማስጠበቅ፤ ሃገሩን ከአምባገነን ገዢዎች ለመታደግ ሲነሳ ሃይማኖት እንደማይከፋፍለው በአገራችን በተደጋጋሚ ያየነው ቢሆንም ሰሞኑን ደግሞ ይህን ኩነት በግብጽ አደባባዮች ስናይ ተደስተናል። የሲቢል መብቶቻቸውን ለማስከበር አደባባይ የወጡ ሞስሊሞች ሲሰግዱ ክርስቲያን ወንድሞቻቸው ሞስሊሞቹን ከአምባገነኑ ቅጥረኞች ሲከላከሉ ተመልክተናል። እንዲሁም እጅግ የበዛው ሰው ሞስሊም በሆነበት የካይሮ አደባባይ ክርስቲያኖች ሥርዓተ ቅዳሴ ሲፈጽሙ አይተናል። የነፃነት፣ የመብት፣ የፍትህ ጥያቄዎች ሁላችንን የሚመለከቱ ጉዳዮች ከመሆናቸውም ባሻገር ከልዩነቶቻችን ይልቅ አብሮነታችን ላይ እንድናተኩር የሚያደርጉን መሆናቸን በካይሮና አሌክሳንድሪያ ያየናቸው ትእይንቶች ያረጋግጡልናል። ህዝብ ለፍትህ፣ ለነፃነትና ለዲሞክራሲ ሲነሳ ከሚለያዩት ይልቅ የሚያስተሳስሩት ነገሮች ይበልጣሉ። አምባነነኖችም ይኸንን ስለሚያውቁ “የሙስሊሞች መብት”፣ “የክርስቲያኖች መብት” እያሉ ሰብዓዊ መብቶችን ሃይማኖታዊ ቀለም ይቀቧቸዋል። ከዚያም አልፎ የአንዱ መብት መከበር የሌላውን መጓደል የሚያመጣ ይመስል ራሳቸውን በመብት አዳይነት ይሾማሉ። አምባገነኖች የእምነት ተቋማትን ህዝቡን ለማከፋፈል ይጠቀሙባቸዋል።

የትግራዩ ገዢ ጉጅሌ የኢትዮጵያን ህዝብ ለመከፋፈል ከሚጠቀምባቸው መሣሪያዎች አንዱ የእምነት ተቋማት ናቸው፤ በጅማ፣ በሃረር፣ በአዲስ አበባ፣ በጎንደርና በደሴ የደረሱ ሃይማኖትን መሠረት ያደረጉ ግጭቶች ሁሉ የወያኔ ከፊል ስውር፣ ከፊል ገሃድ እጅ እንዳለባቸው ጥርጥር የለውም። ኢትዮጵዊያንን በዘር ለመከፋፈል ሞክሮ የጠበቀውን ያህል ውጤት ያላገኘው የትግራዩ ገዢ ጉጅሌ የመጨረሻው እድሉን የሚሞክረው ሃይማኖት ላይ እንደሚሆን እነዚህ አሳዛኝ ክስተቶች አመላካቾች ናቸው።

በአሁኑ ሰዓት የገዢው ጉጅሌ ህዝብን እርስ በርስ የማናከስ እኩይ ሥራ የበለጠ የሰመረ ለማድረግ ካድሬዎቹን በእምነት ተቋማት ውስጥ አሰማርቶ ይገኛል። ወያኔ በሞስሊሙ፣ በኦርቶዶክሱም በፕሮቴስታንቱም የራሱን ካድሬዎች እየመለመለ በየዕለቱ እሳት እየፈጠረ ነዳጅ በመርጨት ሥራ ላይ ተጠምዷል። በዚህም ምክንያት በየማምለኪያው ቦታዎች ከፀሎት ይልቅ በብዛት የሚሰማው አንዱ በሌላው ሃይማኖት ላይ የሚደርጋቸውን ውግዘቶችን እና የክተት ጥሪዎችን ነው።

ወጣቶችን ለመማረክ ሲባልም ጽንፈኛ ቅስቀሳዎችን በመፃህፍትና በሲዲዎች ማሰራጨት ተበራክቷል። በዚህ በፊት ያልነበሩ ልዩነቶች እየተፈጠሩ፤ የነበሩት ደግሞ ከመጠን በላይ ተጋነው እየተወሩ ነው። በዚህም ምክንያት ግብጽ ውስጥ ሞስሊሞችና ክርስቲያኖች በወንድማማችነት አብረው እየፀለዩና ለነጻነታቸውም በጋራ በቆሙበት ወቅት በኢትዮጵያ ቤተ-መቅደሶችና መስጊዶች እየተቃጠሉ ነው። ይህ በአስቸኳይ መቆም ይኖርበታል።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ አላስፈላጊ የሃይማኖት ክርክሮች ቁመው የመለስ ዜናዊን አገዛዝ ለማስወገድ በኅብረት እንነሳ ይላል።

ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!

## በወታደሮቹ ቁጣ የተደናገጡት መለስና ግብረአበሮቹ ወታደሩን ለመደለል እየሞከሩ መሆኑ ተዘገበ

ኢኮኖሚው በከፍተኛ ፍጥነት እያደገ ነው የሚለው መለስና ግብረአበሮቹ በመላ አገሪቱ እየተስፋፋ የመጣው ችግርና የኑሮ ውድነት ያስቆጣውን ወታደሩን ጨምሮ መላውን ይህብረተሰብ ክፍል ለመደለል ሰሞኑን የማትረባ የደመዎዝ ጭማሪ በመስጠት የህዝቡ ቁጣ ለማብረድ የሞከረ ቢሆንም ይህ ግን የህዝቡንና የወታደሩን ልብ ሊያማልል እንዳልቻለ በመታወቁ ልዩ የደመዎዝ ማስተካካየ ለወታደሩ ብቻ ተለይቶ እንዲደረግ መወሰኑንና ተግባራዊ መደረጉን ከውስጥ አዋቂ ምንጮቻችን ለማወቅ ተችሎአል።

ህወሃት ከደርግ ጋር ያደርግ በነበረው ትግል ወቅት ደማቸውን አፍስሠው አጥንታቸውን ከስክሰው የተዋጉትን ነባር ታጋዩች በስም ማጥፋት፤ በሌብነትና በዲስፒሊን ጉድለት ፈርጆ ያባረረው የመለስ ዜናዊ ቡድን አዳዲስ ምልምል ወጣቶችን ከየብሄረሰቡ በኮታ በመመልመል በነደፉት ዘረኛ ፖሊሲ የሥልጣን ዕድሜ ለማራዘሚያ እየተጠቀሙበት ከመሆን አልፎ የገዛ ወገኖቹን በማፈን ለነርሱ ሥልጣን ዕድሜ መራዘም የቆመን ሠራዊት እንደማንኛውም ተራ ኢትዮጵያዊ ወገኖቹ ለአስከፊ ድህነትና የኑሮ ጉስቁልና እንደተዳረገ በሰራዊቱ ውስጥ ግንዛቤ እየተፈጠረ መምጣቱ ለሥር ዓቱ ከፍተኛ ራስ ምታት ሆኖበታል ተብሎአል። ለዚህም ሲባል ለመንግሥት ሠራተኞች ከተደረገው ማስተካከያ በተጨማሪ 22% ልዩ የደመዎዝ ማስተካከያ ለሠራዊቱ ማድረግ እንደተገደደ ለማወቅ ተችሎአል።

በአለማችን በዝርፊያቸው ከሚታወቁት ጥቂት አምባገነን ዘራፊዎች መሃል በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀሱት መለስና አጋሮቹ ከድህው ጎሮሮ ላይ እየነጠቁ የሚሰበስቡትን ገንዘብ በስዊስ ባንኮች እያከማቹ ሳለ ይህ አልበቃ ብሎአቸው ባቁዋቁዋማቸው የንግድ ድርጅቶች ገበያውን በመቆጣጠር የኑሮውን ውዲነት እያባባሱት መሆኑ ለሁሉም ግልጽ የሆነ ጉዳይ ነው። በጉዳዩ ላይ አስተያየት የሰጡን አንድ የፖለቲካ ተንታኝ ሀገራችን ምንም እንኳዋን አለምን የመታት የኢኮኖሚ ቀውስ በጣም ዝቅተኛ በሆነ ደረጃም ሊነካት ቢችልም አብዛኘው በሀገራችን እየደረሰ ያለው ችግር ግን በግንባር ቀደምትነት ሃላፊነት በማይሰማቸው የዘረፋ ቡድኖች ሆን ብለው የሚፈጠሩ ችግሮች ናቸው። በተጨማሪም ችግሩ ስር የሰደደና ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል የነካ ስለሆነ አሁን አገዛዙ እየወሰደው ያለው እርምጃ ሰሞኑን ይነሳብኛል ብሎ ያሰበውን ህዝባዊ አመጽ ለማብረድ በደመነፍስ ያደረገው እርምጃ እንጂ ችግሩን ከስሩ ነቅሎ ለመጣል የታለመ አለመሆኑን አገዛዙ እራሱ ጠንቅቆ ያውቀዋል፤ ተብሎአል። እነመለስ ለኢትዮጵያ የሚቆረቆሩ ቢሆንና የህዝቡን ችግር ከስር ነቅሎ ለመጣል ማድረግ ፈልገው ቢሆን እነሱ ዛሬ በገሀድ ከድሀው ጉሮሮ በመንጥቅ እያካሄዱት ካሉት መጠነ ሰፊ ዝርፊያ በታቀቡ ነበር በማለት አስተያየታቸውን አጠናቀዋል።

ሰሞኑን ፎሪን ፖሊሲ በመባል የሚታወቀው አለም አቀፍ መፅሄት አሜሪካ በአለም ላይ ከመሰረተቻቸው አሳፋሪ ግንኙነቶች ሁሉ ከነመለስ ጋር ያላት አንደኛው ነው በማለት የጠቀሰ ሲሆን ለዚህም አለም አቀፉን ፀር ሽብርተኛ ዘመቻ ሽፋን በማድረግ በራሳቸ ህዝብ ላይ እያደረሱት ያለው እስር፣ ግድያና እጅግ ገሀድ የወጣውን ዘረፋ ሀገሪቱን ወደ ማትንሰራራበት ውድቀት ላይ እያደረሳት መሆኑን ጠቅሶአል። ለዚህም አሜሪካንን ጨምሮ ሌሎች መራብያውያን ሀገራት ከንዲይ አይነት አምባገነኖች ጋር መወገን የሚያደርስባቸውን ውርደት ከቱኒሲያና ከግብጽ በመማር ከህዝቡ ጋር እንዲወግኑ ኣሣስቦአል።

### ህዝባዊ አመጽ እንደሚነሳበት ስጋት የገባው . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

በተያያዜ ዜና ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ በተደጋጋሚ እያደረገ ያለው የብር ምንዛሪን አቅም የማውረድ ርምጃ አሁንም የገበያ ዋጋ ግሽበትን እያባበሰ እንደሆነ ብሉምበርግ የዜና አውታር ባወጣው ዘገባ ላይ አሳይትዋል። እንደ ብሉምበርግ የዜና አውታር የኢትዮጵያ የዋጋ ግሽበት በቅርብ ቀን ከደረሰበት የአስራ አራት ነጥብ አምስት በመቶ ወደ አስራ ሰባት ነጥብ ሰባት በመቶ ማሻቀቡን አስታውቁአል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ የምግብ ዋጋ ከነበረበት የዋጋ ውድነት ደረጃ አሁንም የአስራ ሶስት ነጥብ ስድስት በመቶ እንዲሁም የምግብ እህል ባልሆኑ ሸቀጦች ላይ ደግሞ የሃያ ሶስት ነጥብ ሰባት በመቶ ጭማሪ ማሳየቱን ጨምሮ አስታውቁአል።

ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ በኢትዮጵያ ህዝብ ከደረሰበት የተጠራቀመ ጥላቻ የተነሳ ህዝባዊ አመጽ ሊነሳብኝ ይቿላል ብሎ በመስጋት ሸማቹን ህብረተሰብ ለማስደሰት ከአቅርቦት ጋር በፍጹም የማይጣጣም የዋጋ ተመን በቅርቡ እድርጎ እንደነበረ ይህም ዋጋ ማስተካካያ የተደረገባቸውን የፍጆታ ዕቃዎች ከገቢያ ላይ እንዲጠፉ እንዳደረገው ህዝብ በቅሬታ እየተናገረ ነው።

## አሳፋሪ ከሆኑት የአሜሪካን አጋሮች መካከል፤ አንዱዋ ኢትዮጵያ መሆንዋ ተገለጸ

ዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ በአለም ዙሪያ ከምታደርገው ዲፕሎማቲክ ግንኙነት ኢትዮጵያን ጨምሮ ከ8 አገሮች ጋር ያላት ወዳጅነት እጅግ የሚያሳፍር እንደሆነ ፎሪን ፖሊሲ በመባል የሚታወቅ አንድ በአሜሪካን አገር የሚታተም መጽሄት ዘገበ። ከ2 ቀን በፊት በፈረንጆች አቆጣጠር ጃንዋሪ 31 ለንባብ የበቃውን ይህንን ዘገባ ለህዝብ ይፋ ያደረገው ፎረን ፖሊሲ የሚል ድህረ ገጽ እንደገለጸው በጸረ ሽብርተኝነት ሥም የቡሽ አስተዳደር ከኢትዮጵያው ዘረኛ አገዛዝ ቁንጮ መለስ ዜናዊ ጋር የመሰረተቺው ወዳጅነት ለአሜሪካ እጅግ አሳፋሪ ከሆኑት አንዱ እንደሆነና ቡሽን የተኩት አዲሱ ፕሬዝደንት ኦባማም ቢሆኑ ግንኙነቱን አለዘቡት እንጂ አልቀየሩትም ሲል ተችቶአል። ፎሪን ፖሊሲ እንደ ኢትዮጵያ ሁሉ አሳፋሪ ናቸው ያላቸውን ሌሎች ሃገራትም የዘረዘረ ሲሆን እነዚህ ሃገራትም ሳውዲት አረብ፣ የመን፣ ዮርዳኖስ፣ ዩጋንዳ፣ አዝበኪስታን፣ ካዛኪስታንና ቬትናአም መሆናቸውን ገልጹአል።

ፎሪን ፖሊሲ አሳፋሪ ናቸው ያላቸውን አገራት መሪዎች ተግባራት በዝርዝር ያወጣ ሲሆን ሁሉም በየአገራቸው የዜጎቻቸውን ሰብአዊ መብት ከመጣስ ጀምሮ በሙስናና በሥልጣን ብልግና የሚታወቁ ናቸው ብሎአቸዋል። የመለስ ዜናዊን ተግባር በልዩ ሁኔታ የዘረዘረው ፎረን ፖሊሲ ባለፈው ግንቦት ወር 2002 በተካሄደው ምርጫ የወያኔው አምባገነን አገዛዝ 99.6 በመቶ በሚሆን ውጤት አሸንፊያለሁ በማለት ማሳወቁን፣ ይህንም ተከትሎ በኢትዮጵያ የነበረው እጂግ ዝቅተኛ የሰብአዊ መብቶች ጥበቃ ጭራሹን መጥፋቱን እንዲሁም የተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች በሃገሪቱ የፖለቲካ ስራን ለመስራት የሚችሉበትን ሁኔታ ጭራሹን እንደዘጋው ገልጹአል።

ፎሪን ፖሊሲ በኢትዮጵያ እጂግ በርካታ ንጹሃን ዜጎች እንዲሁም በርካታ የተቃዋሚ ፓለቲካ ፓርቲ አባላት ያለበቂ ምክንያት እየታፈሱ ወደ እስር ቤት እንደሚወሰዱ እንዲሁም በእስረኞች ላይ የወያኔው አገዛዝ እያደረሰ ያለውን እስራትና በደል በዝርዝር አስቀምጡአል። ከዚህም በተጨማሪ መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋአማት ላይ የወያኔው አምባገነን አገዛዝ የወሰዳቸውን ተገቢ ያልሆኑ ርምጃዎችን፣ በነጻ ሚዲያ ተቋአማትና ጋዜጠኞች ላይ እየተወሰዱ ያሉ አፋኝ ርምጃዎችን በሙሉ በዝርዝር አስቀምጡአል። ፎሪን ፖሊሲ በዚህም ምክንያት በአሜሪካን ሃገር የሚገኘው ፍሪደም ሃውስ ኢትዮጵያን ቀደም ብሎ በከፊል ነጻ የሆነች እያለ ይጠራበት ከነበረው ደረጃ ከአፈና ፍጹም ነጻ ያልሆነች ሃገር ወደሚለው ደረጃ እንድትወርድ ማድረጉን ጠቁሙአል።

በዘገባው አሜሪካ በኢትዮጵያ እየተካሄደ ያለውን አፈና በግልጽ የምታውቅ በመሆንዋ የወያኔው አገዛዝ በሰባዊ መብቶች ላይ የሚያካሂደው አፈና ተገቢ እንዳልሆነ ወቀሳ እየሰነዘረች እንደሆነ ቢታወቅም፣ ለሰብአዊ ርዳታ በማለት የምትልከው ገንዘብ ለፖለቲካ ፍጆታ እየዋለ እንደሆነ መረጃው እንዳላት ቢታወቅም በየዓመቱ ወደ ስድስት መቶ ሚሊዮን የአሜሪካን ኦላር ማለትም ወደ አስር ቢሊዮን የኢትዮጵያ ብር የሚጠጋ ገንዘብ አሁንም መለገስ መቀጠሉዋ የሚያሳፍር ነው ብሉዋል።

### የወያኔ ካድሬዎች ከፌዴራል ፖሊሶች ጋር በመሆን . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

የተጀመረው ህዝባዊ አብዮት የመለስ ዜናዊን ዘረኛ አገዛዝ ጠራርጎ እንዳያስወግድ የመከላከል ሩጫ የጀመረው ወያኔ፤ ለወጣቶቹ የተገባላቸውን የማዘናጊያ ተስፋ ተግባራዊነት የሚከታተል ከሶስቱም የአዲስ አበባ ዞኖች አምስት አምስት ወጣቶችን በመመልመል ባጠቃላይ 15 አባላት ያሉበት ቡድን እንዲቋቋም አድርጎአል በደረሰን ዘገባ መሠረት።

ወያኔ ህዝባዊ ተቃውሞን ከቻለ በማስፈራራት ካልቻለ ደግሞ በጥቂት ጥቅማጥቅሞች ሰዎችን በመደለል ለማክሸፍ እንደሚሞክር በድህረ ምርጫ 97 የታየ ሲሆን የሥራ ማቆም አድማ አድርገው የነበሩ የታክሲ ሾፌሮችን ለማንበርከክ በቁጥር ጥቂት የሚሆኑ የታክሲ ተራ አስከባሪዎችን " የትራፊክ ህግን ለማስከበር" በሚል ሽፋን በማደራጀት በጉዋደኞቻቸው ላይ እንዲሰልሉ እንዳደረገና ያም በተነሳው ህዝባዊ ተቃውሞ ውስጥ ታክሲ አሽከርካሪዎች የጎላ ሚና እንዳይጫወቱ እንዳሸመደመደ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው።

በግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ የህዝብ ግንኙነትና ቅስቀሳ ዘርፍ በሳምንት አንዴ የሚዘጋጅ ድርጅታዊ ልሳን

የፖስታሳጥን ቁጥር ፦ POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

## እስከዛሬ ድርጅቶቻችን ውጤታማ ለምን አልሆኑም? ግንቦት7ስ በምን ይለያል? (ዶ/ር ታደሰ ብሩ) ክፍል 1

ክቡራትና ክቡራን በዛሬው እለት በመካከላችሁ ተገኝቼ የእስካሁን የድርጅት ልምዶቻችንን በተመለከተ ያለኝን ጥቅል ሃሳብ እና ስለ ግንቦት 7፡ የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ድርጅታዊ ይዘት እንድናገር እድል ስለተሰጠኝ ከልብ አመሰግናለሁ። የዛሬ ሶስት ሳምንት እስሎ ውስጥ "ወደፊት መራመድ እንዴት አቃተን? ለወደፊቱስ ምን ማድረግ እንችላለን?" በሚል ርዕስ ባለፉት ሃምሳ አመታት ጊዜ ውስጥ የረባ ለውጥ ለማምጣት ያልቻልንባቸው ምክንያቶች ናቸው ብዬ የማምንባቸውን ሰባት ነጥቦችን አንስቼ ነበር። ያ ንግግሬ ያተኮረው እኛ ኢትዮጵያዊያን በግለሰብ ደረጃ ባሉብን ችግሮች እና ችግሮቹንም ለማስወገድ ይጠቅሙን ይሆናል ብዬ ባሰብኳቸው ጉዳዮች ላይ ነበር።

የዛሬው ንግግሬ የዚያው ተከታይ ቢሆንም ትኩረቱ ግን ድርጅት ግንባታ ላይ ይሆናል። ለለውጥ የግለሰብ ተነሳሽነት አስፈላጊ ቢሆንም እንኳን ማኅበራዊ ለውጥ በአንድ ወይም በጥቂት ግለሰቦች ጥረት ብቻ አይመጣም። *"አንድ" ታላቅ ውጤት ለማስገኘት የሚበቃ በጣም ትንሽ ቁጥር ነው ይባላል* /one is too small a number to achieve greatness/ ለታላቅ ውጤት መተባበር ግዴታ ነው። ሆኖም ግን መተባበርን በቅስቀሳ፣ በሰበካና በልመና የምናመጣው ነገር አይለም። ሰዎች መተባበር የማይፈልጉባቸው በርካታ ምክንያቶች አሉ። ዛሬ እነሱ ውስጥ አልገባም።

ዛሬ ልናገር የምፈልገው ብዙ ቅን አሳቢ መካሪዎች የሚረሱትን ነገር ነው። ሰዎች እውቀታቸውንና ጉልበታቸውን የሚያስተባብሩበት ድርጅት ካልፈጠሩ በጋራ የመሥራት አስፈላጊነት መቀበላቸው ብቻውን እምብዛም ፋይዳ የለውም። ችግሩ ድርጅት በመፍጠር ላይም አያበቃም። የሚፈጠረው ድርጅትም የታለመውን እቅድ ማሳካት የሚችል ውጤታማ ተቋም ማድረግ ከባድ ሥራ ነው። እንዲያውም እኛ ኢትዮጵያዊያን ድርጅትን በተመለከተ የገጠመን ዋነኛ ችግር ይህ ነው ብዬ አስባለሁ። በጋራ ለመሥራት ተስማምተን የመሠረትናቸው ድርጅቶች አይናችን ስር ሲሽመደመዱ አንዳዶቹም ሲፈረካከሱ እናያለን። ስለሆነም "እንደምን ጠንካራ ድርጅት መፍጠር እንችላለን?" በሚል ርዕስ ጉዳይ ላይ መወያየት በጣም ጠቃሚና ወቅታዊም ነው ብዬ አምናለሁ።

ድርጅት ወደ አንድ የፈለግንበት ግብ መድረሻ መሣሪያ እንጂ በራሱ ግብ አይደለም። ድርጅት እንደ መኪና ከአንድ ቦታ ወደ ምንፈልገው ሌላ ቦታ በፍጥነት እንድንደርስ ያግዘናል። ከፋቱ አንዳንዶች ተሳፋሪዎች ልባቸው እመድረሻቸው ላይ ይሆንና ለጊዜው የሚገኙት መኪና ውስጥ መሆናቸውን ይረሱታል። ሌሎቹ ደግሞ የመኪናውን ጉዞ የዘወትር ሕይወታቸው ያደርጉታል። አንድ ለለውጥ የተዘጋጀ ድርጅት አባል ሁለቱንም ዓይነት ተሳፋሪዎች መምሰል የለበትም።

የመጀመሪያዎቹ መኪና ውስጥ መሆናቸውን መርሳታቸው አሰቡበት ከመድረስ ሊያግዳቸው ይችላል፤ የሚጓዙበትን መኪና ባግባቡ መፈተሽ፣ መጠራረግ፣ መጠጋገን፣ ቅባትና ነዳጅ መስጠት ያስፈልጋል፤ ከሁሉም በላይ ብቃት ባለው አሽከርካሪ መኪናው በጥንቃቄ መነዳት አለበት። አለበዚያ መኪናው ሊሰናከል ይችላል፤ ከከፋም መገፊያቸው ሊሆን ይችላል። ድርጅትም እንደዚሁ ነው። አንድ ድርጅት አባላቱ አሰቡበት እንዲያደርሳቸው በየጊዜው መፈተሽ፣ መጠረግ፣ መጠገን እና መወልወል አለበት። ከሁሉም በላይ ደግሞ ድርጅቱ ብቃት ያለው አመራር ማግኘቱ መረጋገጥ ይኖርበታል። አለበዚያ ድርጅቱ አባላቱን አሰቡበት ማድረስ አይችልም።

የመኪናውን ጉዞ የዘወትር ሕይወታቸው ያደረጉት ደግሞ የሚጓጉለት የተለየ መድረሻ የለምና መኪናው ሲዞር ቢከርም ችግር የለባቸውም። እነሱ ወይ ሾፌር፣ አለያም ረዳት፣ ወይም ዝም ብሎ ተሳፋሪ ብቻ በመሆን የዘወትር ኑሮዓቸውን መኪና ውስጥ ይኖራሉ። ድርጅትም ውስጥ እንደዚሁ ነው። ዓላማን ማሳኪያ መሣሪያ ወይም መታገያ በመሆን ፋንታ ድርጅትን ኑሮዓቸው ያደረጉ ሰዎችም አሉ። አንዳንዶች እድሜ ልካቸውን መሪ፣ ሌሎች ደግሞ እድሜ ልካቸውን ተመሪ ሆነው ይኖራሉ። ድርጅቱ አንዳችም ውጤት ባያስገኝ አይከፋቸውም - ድርጅታቸው መደበሪያቸው ነው።

እኛ ኢትዮጵያዊያን ስለ ድርጅት ያለን እውቀትና ልምድ በጣም፣ እጅግ በጣም ውስን ነው። የፓለቲካ ፓርቲዎች የመደራጀታቸው ዜና ተወርቶ ሳይጠገብ የመሰነጣጠቃቸው መርዶ ይከተላል። በአለፉት አርባ አመታት ፓርቲዎች በአንድ በኩል እርስ በርሳቸው ሲበላሉ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ታርቀው ሲሰባሰቡ እና መልሰው ተጣልተው ሲፈረካከሱ ቆይተዋል። "ኢትዮጵያዊያን አብረን መብላት እንጂ አብረን መሥራት አንችልበትም" የሚለውን አባባል እኔ በበኩሌ እስኪሰለቸኝ ሰምቸዋለሁ። በአንድ ስብሰባ ላይ "ኢትዮጵያ በሩጫ ክብረ ወሰኖችን እየያዘች ለምን በእግር ኳስ ወደኋላ ቀረች?" ተብሎ ለተነሳው ጥያቄ አንዱ የሰጠው ምላሽ

> *በሩጫ በመጀመሪያዎቹ ዙሮች ከተደጋገፍክ ትልቅ ነገር ነው የፍፃሜው ዙር ላይ ግን ሩጫ የግል ነው። ይህ ለኢትዮጵያዊያን ይመቻል። እግር ኳስ ግን ጎሏ ሥር እንኳን ሆነን ካንተ የተሻለ እድል ላለው ጓደኛህ ማቀበል አለብህ። ደግሞም እስከ መጨረሻዋ ሰከንድ ከቡድን ጓደኞችህ ጋር መደጋገፍ አለብህ። ይኼ ጨዋታ ለኢትዮጵያዊያን ፈፅሞ አይመችም* - የሚል ነበር።

ይኸንና የመሳሰለውን ስሰማ 'እኛ ኢትዮጵያዊያን ለተደራጀ ሥራ አንመችም' የሚለውን ሃሳብ ለመቀበል ራሳችንን ያዘጋጀን ይመስለኛል። ለጋራ ጥቅም ተባብረንና ተደራጅተን የመሥራት ችግራችን አሁን አሁን በሁሉም የኑሮዓችን ዘርፎች እየታየ ነው። የሽርክና ንግዶች ኢትዮጵያ ውስጥ እድሜዓቸው በጣም አጭር ነው። በሃይማኖት ተቋማት እንኳን ሳይቀር መሰንጠቅ፣ አንጃና ተለጣፊ ተለምዷል። ይህ ከባድ አደጋ ነው። ለመሆኑ እንዲህ ዓይነት ችግር ያለው እኛ ዘንድ ብቻ ነው? አይደለም። የመደራጀት ችግር ሁሉም አገር ውስጥ አለ። እኛ ዘንዳ ግን በዝቷል። ማደራጀት የሥራ አመራር /ማኔጅመንት/ ክህሎት አካል ነው። የማደራጀት ብቃት ማነስ የማኔጅመንት ብቃት ማነስ አንዱ መገለጫ ነው።

በድርጅቶች ወይም በቡድኖች እድገት ውስጥ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ አምስት ዋና ዋና እርከኖች አሉ። እነርሱም 1ኛ) የምስረታ ወቅት/Forming stage/ 2ኛ) የመናጥ ወቅት /Storming stage/ 3ኛ) የመስከን ወቅት /Norming stage/ 4ኛ) የመከወን ወቅት/ Performing stage/ እና 5ኛ) የመሻሻል ወቅት/Reforming/Transforming stage በመባል ይታወቃሉ።

እነዚህ አምስት እርከኖች የግድ በዚሁ ቅደም ተከተል ይከሰታሉ ማለት አይደለም። ጉዞው ወደላይ ብቻም አይደለም ወደ ታች ማሽቆልቆልም አለ። አንድ ድርጅት በሁሉም እርከኖች ላይ የግዴታ ማለፍ አለበት ማለትም አይደለም። ቀደም ብዬ እንዳነሳሁት የመመሥረታቸው ብሥራት ተከትሎ በመጣ መናጥ የተበታተኑ ድርጅቶችን እናውቃለን። ሰፊ የሕዝብ መሠረት ከያዙ በኋላ ተንሸራተው ወደኋላ በመመለስ ተበጣብጠው የተከፋፈሉ ድርጅቶችም አሉን። የሆነ ሆኖ የኢትዮጵያ ድርጅቶችን አንድ የጋራ ባህርይ አውጣ ብባል **በመናወጥ ወቅት የሚያሳዩት እጅግ ደካማ የቅራኔ ማኔጅመንትን** ነጥዬ አወጣለሁ። በዚህም ምክንያት የመናጥን ወቅት /storming stage/ ትንሽ ዘርዘር አድርገን ብናየው ለግንዛቤዓችን ይረዳል ብዬ አምናለሁ።

የመናጥ ወቅት ስሙ ራሱ እንደሚገልፀው ድርጅቶች በቅራኔዎች የሚበጠበጡበት ወቅት ነው። በምሥረታ ጊዜ የነበረው ጨዋነት በዚህ ወቅት አይኖርም። በመስከን ወቅት እንዳለው ዓይነት በሀጎችና ደንቦች መገዛት በዚህ ወቅት የለም። የጠቦች መነሻ ምክንያቶች በጣም ብዙ መስለው ቢታዩም አስተውሎ ላጠናቸው ከአምስት መሠረታዊ ጉዳዮች ውጭ አይደሉም። እነሱም 1ኛ/ የአባላት የግል ባህሪይ 2ኛ/ የአባላት የእርስበርስ ግኑኝነት 3ኛ/ በድርጅቱ ዓላማና ግቦች ላይ የሚነሱ ጥርጣሬዎች 4ኛ/ የድርጅቱን ደንቦችና መመሪያዎችን ጥሰሃል አልጣስኩም ክርክሮች እና 5ኛ/ ከሌሎች ድርጅቶች ጋር በሚደረጉ ግልጽም ሆነ ስውር ግኑኝነቶች ወይም ጥርጣሬዎች ናቸው። በመናጥ ወቅት "እነዚህ ሰዎች አብረው መሆን አይችሉም" እስከሚባል ድረስ አባላት እርስበሳቸው ላይግባቡ ይችላሉ።

ቅራኔ የእድገት ምንጭ ነውና "መናጥ" የግድ መጥፎ ነገር አይደለም። ሆኖም መናጥ ወደ ተሻለ ውጤት እንዲያመራ ሁለት ቅደም-ሁኔታዎች መሟላት አለባቸው። እነዚህም ጊዜ እና ጥበብ ይሰኛሉ። የረጋ ወተት ቅቤ እንደሚወጣው ሁሉ የተደራጀ ደንብና መመሪያ ያላቸው እና ድርጅታዊ ባህልን ያዳበሩ ድርጅቶች ቢናጡ የበለጠ ተጠናክረው ሊወጡ እንደሚችሉ ተስፋ ማድረግ ይቻላል። ትኩስ ወተት ቢናጥ ምን ይወጣዋል? ድርጅቶችም እንደተቋቋሙ ከተናጡ መፍረሻቸው ሊሆን ይችላል። ሁለተኛው ቅድመ ሁኔታ "ጥበብ" የተሰኘው ሲሆን በተለይም የቅራኔ አፈታት ጥበብን ይመለከታል። ይህ ጥበብ በትምህርትና ስልጠና ሊገለበት ቢችልም ባህላዊ ገጽታው የጎላ ነው። እኛ በትምህርትና ስልጠናችን ጎደሎነት ይሁን በባህላችን (ለምሳሌ ዘራፍ! ካፈርኩ አይመልሰኝ) ወይም በሁለቱም ምክንያቶች አላውቅም የቅራኔ አፈታት ክህሎታችን በጣም ዝቅተኛ ነው። ይህ ክህሎት ደግሞ በዘመናዊውና ከተሜው ትውልድ ዘንድ የባሰ አሽቆልቁሏል። በዚህም ምክንያት ድርጅቶች የማዕበሉን ወቅት መሻገር አቅቷቸው ተደነቃቅፈውና ተሽመድምደው ይቀራሉ። የአርባ አመታት የኢትዮጵያ የፓለቲካ ድርጅቶች ታሪክ ባጭሩ የሚከተለው ይመስላል ....

> *እከሌ የሚሉት ድርጅት ተወለደ፣ አደገ፣ ገነነ። የእከሌ ድርጅት መሪዎች ተጣሉ። አረ እንዲያውም ተከፋፈሉ። እከሌ ድርጅት ደከመ። አሁንስ አለ አይባልም ነፍሱ ግን አልወጣችም።*

ክብራትና ክቡራን ወያኔስ? ትሉ ይሆናል። የወያኔ ታሪክ ከሌሎቹ የባሰ ነው። ወያኔ በተደጋጋሚ በቅራኔ የታመሰ ሲሆን ከእያንዳንዱ መታመስ በኋላ ከፋት እያሸነፈ የወጣበት ድርጅት ነው። በ1970 ዎቹ በደረሰበት ኃይለኛ መናጥ ሲቪክ ባህሪውን አጥቶ በጥቂት ሰዎች ወደሚመራ የማፍያ ድርጅትነት ዘቅጧል። ወያኔ አንድም መናጦችን በሞገስ ተወጥቶ አያውቅም። የመናጥን ወቅት በክብርና በሞገስ የተወጣ አንድም ኢትዮጵያዊ የፓለቲካ ድርጅት የለም።

ክቡራትና ክቡራን

ከላይ በአጭሩ እንደገለጽኩት ድርጅቶችን ሲበጥበጡና ሲያፈርሱ የቆዩ መሠረታዊ ምክንያቶች በአምስት ዋና ዋና ክፍሎች መመደብ ይቻላል።

1. የግለሰብ አባላት በተለይም የፓርቲ መሪዎች ተክለ ሰውነትን /personality/ የተመለከቱ ጉዳዮች፤
2. የአባላት የእርስ በርስ ግኑኝነት ማለትም የሳይኮ-ሶሻል ጉዳዮች፤
3. የድርጅቱን ርዕይ፣ ተልዕኮና ግብ የተመለከቱ ጉዳዮች፤
4. የድርጅቱ ደንቦች፣መርሆዎችና አፈፃፀማቸውን የተመለከቱ ጉዳዮች፤ እና
5. የውጭ ግኑኝነት ማለትም ድርጅቱ ከሌሎች ድርጅቶች ጋር ሊኖረው ስለሚገባው ግኑኝነት በተመለከተ የሚነሱ ቅራኔዎች ናቸው።

በጣም በአጭሩ እያንዳንዱን በየተራ እንድናያቸው ፍቀዱልኝ።

### የግለሰቦች የስብዕና ችግር

ግንዛቤ /perception/ ከእውነታ /fact/ በላይ የሚሆንበት ጊዜ አለ። ሰዎች ነጩን ነገር ጥቁር ነው ብለው ካመኑ ማስረጃ አይመልሳቸውም። የሰዎች ግንዛቤ በብዙ ምክንያቶች ሊዛባ ይችላል። እድሜ፣ የሥራ ጫና፣ ወከባ፣ አሉባልታ፣ ሃሜት፣ ውሸት፣ ጥቃማ ጥቃሞች እና የማመዛዘን ችሎታ ማጣት የግንዛቤ አቅምን ያዳክማሉ። ሳባባቢያችን በግንዛቤዓችን ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ አለው። ሰዎች በተዛባ ግንዛቤ መነሻነት የሚወስዱት እቋም በድርጅቱ ላይ ከፍተኛ ኪሳራ ሊያደርስ ይችላል። በተለይ ግለሰቡ የድርጅቱ መሪ ከሆነ ጉዳቱ እጅግ ከፍተኛ ይሆናል።

ኢትዮጵያ ውስጥ የፓለቲካ ድርጅቶች ከራሳቸው ስም ይልቅ በመሪዎቻቸው ስም ይታወቃሉ። ብዙዎቹ የእከሌ ፓርቲ እየተባሉ ይጠራሉ። ድርጅቱ እንደ መሪው ሁሉ ብሔር (ወይም ብሔረሰብ)፣ እድሜ፣ የትምህርት ደረጃ ... ወዘተ ይኖረዋል። ድርጅቱ እንደ መሪው ሁሉ ባህሪም ይላበሳል። አንዳንዱ ድርጅት ቁጡ ነው፤ ሌላው መሰሪ። አንዳንዱ ችኩል፣ አንዳንዱ ቀርፋፋ ነው። ይህ ሁሉ ነገር ውሎ አድሮ በድርጅቱ ውስጥ ቅራታን መፍጠሩ እና በጊዜው የእርምት እርምጃ ካልተወሰደበት ደግሞ አንድ ቀን መፈንዳቱ አይቀርም። (ክፍል 2 መሚቀጥለው ሳምንት ይቀጥላል)

## ህንድ ከኢትዮጵያ ወደ ሁለት ሚሊዮን ሄክታር የሚጠጋ ለም መሬት መውሰዱአ ታወቀ

ኢትዮጵያ ለህንድ በሊዝ ኪራይ የሰጠቺው ወደ ሁለት ሚሊዮን ሄክታር የሚጠጋ ለም መሬት ህንድ የዜጎቹዋን የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ እያከናወነች ላለው ተግባር ትልቅ አስተዋጾ ይኖረዋል በማለት ኢኮኖሚክ ታይምስ በመባል የሚታወቅ ጋዜጣ ዘገበ::

ኢኮኖሚክ ታይምስ በመባል የሚታወቀው ጋዜጣ ባወጣው ጽሁፉ ኢትዮጵያ ለህንድ እስካሁን 1.8 ሚሊዮን ሄክታር ለም መሬት በሰባ ዓመታት የሊዝ ኪራይ ማስረከቡዋንና ይህም ለህንዳዊያን የምግብ ዋስትና መረጋገጥ ከፍተኛ ሚና እንደሚኖረው ገልጹአል:: ዘገባው ይህ ከኢትዮጵያ የተገኘ ድንግል የእርሻ መሬት ከፍተኛ የግብርና ሰብል አምራች የሆነቺውን የፑንጃብ ክፍለግዛት 50 በመቶ የሚሆነውን የቆዳ ሽፋን የሚሸፍን እንደሆነና ይህም ህንድ 25 ከመቶ የሆነውን የሩዝ ፍጆታዋን የምታገኝበት እንደሆነ ከዚህም የተነሳ የህንድ ባለስልጣናት ከፍተኛ ደስታ እንደተሰማቸው ዘግቡአል::

የመረጃ ድረገጹ በህንድ አገር ጉብኝት እያደረገ ያለውን የኢትዮጵያ ግብርና ሚንስትር ተፈራ ደርበውን በመግለጽ እንደዘገበው የወያኔ አገዛዝ እስካሁን ድረስ ለህንድ ሃገር ቃል ከገባውና ካስረከበው የለም መሬት ሽያጭ በተጨማሪ ለውጭ ሃገራት ኢንቨስተሮች ለመሸጥ ካዘጋጀው ተጨማሪ 3.6 ሚሊዮን ሄክታር መሬት ውስጥ የህንድ ኢንቨስተሮች የፈለጉትንን ያህል ቢወስዱት ወይንም ሙሉ በሙሉ ጠቅልለው ቢይዙት ደሳታቸው እንደሆነ መግለጹን አያይዞ ዘግቦአል።

ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ በኢትዮጵያ የተሻሉና ለም በሆኑ ክልሎች የሚገኘውን ሰፋፊ የርሻ ቦታ በአካባቢው የሚገኙ አርሶ አደሮችን በማፈናቀል የመሬት ሽያጩን የጥድፊያ ዘመቻ በስፋት እንደቀጠለበት ስንዘግብ መቆየታችን አይዘነጋም:: ከዚሁ ጋር ተያይዞ በግዳጅ ከቀያቸው እየተፈናቀሉ የሚገኙት አርሶ አደሮች ጥያቄ ሲያነሱ እስከ ሞት ድረስ የሚደርስ እንግልት እንደሚጠብቃቸው መግለጻችን ይታወሳል::

### መለስ ዜናዊ በሙኒክ ጀርመን ከፍተኛ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

የኢትዮጵያዊያን ወንድሞቻቸውን ሠልፍ በመቀላቀል ጸረ መለስ ዜናዊን መፈክር በጋራ ሲያስተጋቡ እንደዋሉ በምስል የተደገፈ ዘገባ እንዳቀረበ ለማወቅ ተችሎአል።

መለስ ዘናዊ ከድህረ ምርጫ 97 ጀምሮ በየሄደበት ታላላቅ ተቃውሞዎች ሲገጥሙት እንደኖሩና በፈረንጆች አቆጣጠር ዲሰምበር 2006 ዓም በብራስል ከተማ ተዘጋጅቶ በነበረው የአፍሪካ መሪዎች ስብሰባ ላይ ከአዳራሹ ዘልቀው የገቡ ኢትዮጵያዊያን መለስ ዜናዊ ለንግግር መድረክ ላይ እንደወጣ የኢራቁ ሳዳም ሁሴንና መለስ ዜናዊ አንድ ናቸው ፍርድ ይገባዋል በማለት መፈክር ማስተጋባት ሲጀምሩ በድንጋጤ ብዛት ለ20 ደቂቃ የተሰጠውን ንግግር ማጠናቀቅ ተስኖት አንዳቋረጠ በመድረክ ላይ ሆኖም እጅና ከንፈሩ ሲንቀጠቀጥ እንደተስተዋለ በወቅቱ መዘገቡ ይታወሳል።

በተያያዜ ዜና በአምባገነኑና ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ግፍና በደል እናት ሃገራቸውን ለቀው በስደት ኖርዌይ የሚገኙ በርካታ ኢትዮጵያዊያን የኖርዌይ መንግስት የስደተኝነት ጥያቄአችንን በአግባቡ አላስተናገደም በሚል ከፍተኛ የተቃውሞ ሰልፍ ማድረጋቸውን ዘጋቢያችን ከኦስሎ ኖርዌይ ባስተላለፈልን ዘገባ ገለጸ:: ሰልፈኞቹ የወያኔውን አምባገነን አገዛዝ ዘግናኝ ድርጊቶችና ጭፍጨፋዎች የሚገልጹ ፎቶግራፎችን እንዲሁም መፈክሮችንም መያዛቸውም ታውቁአል::

ኢትዮጵያዊያኑ ስደተኞች በተለይም በኦስሎ ከተማ ባካሄዱት ሰልፍ የአምባገነኑንና ዘረኛውን መለስ ዜናዊ እንዲሁም የበረከት ስም ኦን፣ አዜብ መስፍንና ሌሎችንም የአምባገነኑ ስርአት ቁኘጮዎች ፎቶግራፎቻ ኦስሎ ከሚገኘው የኖርዌይ ፓርላሜንት ጽ ቤት ፊት ለፊ በእሳት ማቃጠላቸው ታውቁአል::

እንደዘጋቢያችን ሪፖርት ኢትዮጵያዊያኑ በኖርዌይ ያደረጉት ሰላማዊ ሰልፍ በዋነኛነት በኦስሎ ከተማ ሲሆን ከዚህም በተጨማሪ በተለያዩ የኖርዌይ ከተሞችም ጭምር መሆኑን ለማወቅ ችለናል:: በኦስሎ ከተማ በተካሄደው ሰልፍ ከአምስት መቶ በላይ የሚሆኑ ሰልፈኞች የተገኙ ሲሆን ሰልፈኞቹ ከፖልኪሶች ጋርም መጋጨታቸው ታውቁአል:: ይሁን እንጂ ከፖሊስ ጋር በተደረገው ግጭት የደረሰው ጉዳት አለመኖሩን ዘጋቢያችን ጨምሮ ገልጹአል::

ከዚሁ ጋር ተያይዞ በደረሰን ዘገባ ኢትዮጵያዊያኑ ስደተኞች በኦስሎ ከተማ ሰላማዊ ሰልፍ ካካሄዱ በሁአላ አንድ ቤተክርስቲያን ውስጥ በመግባት ከቤተክርስትያኑ አንወጣም ማለታቸውንና የኖርዌይ መንግስት ተገቢዉን መልስ የማይሰጣቸው ከሆነ ጥያቄአቸውን ማቅረብ እንደሚቀጥሉ በመግለጽ የረሃብ አድማ ላይ እንደሚገኙ ዘጋቢያችን ባስተላለፈልን ሪፖርት አስታውቁአል::

ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ ኢትዮጵያ ላይ እያደረሰ ባለው ጥፋት ምክንያት እጂግ በርካታ ኢትዮጵያዊያን ለስደት እንደሚዳረጉ በዚህም ምክንያት ኢትዮጵያ በስደተኞች ብዛት የቀዳሚነት ስፍራን እየያዘች መምጣቱአን መዘገባችን ይታወሳል::

### ሙባረክ ከስልጣናቸውን ለቀቁ፣ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ላለፉት ሰላሳ ዓመታት የማይደፈር ይመስል የነበረውን የሙባረክን እንደብረት የጠነከረ -ሥልጣን ገዝግዞ የበጠሰው ህዝባዊ አመጽ የዋሽንግተን መሪዎችን ጨምሮ የበርካታ ም ዕራባዊያን ሃገራትን አቋም ማስለወጡም በስፋት እየተዘገበ ነው። ይሁን እንጂ ለድፍን ሠላሳ አመት ለሙባረክ ሥርዓት ፅናት ድጋፍ ስትሰጥ የቆየቻዉን ዩናይትድ ስቴትስን ጨምሮ ምእራባዊያን ሃገራቱ ሙባረክ ሃገር ጥለው መኮብለላቸው የማይቀር እንደሆነ እያወቁ ሙባረክን ዳር ዳር ከማለት ባለፈ ሙባረክ ሥልጣን እንዲለቁ አለመናገራቸው መነጋገሪያ አጀንዳ ሆኖ ሰንብቱአል::

ምዕራባዊያን አገሮች ለረጅም አመታት ዋና ሸሪካቸው አድርገውት የኖሩትን የግብጹን ፕረዚዳንት ሞሃመድ ሁሴን ሙባረክ ሥልጣን በለቀቁ አንድ ሰዓት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የሲውዚ መንግሥት ሙባረክ ከህዝባቸው ሰርቆ በአገሩ ባንኮች ያኖረውን ገንዘብ በሙሉ እንዳይነቀሳቀስ ማገዱን አስታውቆአል። ይህ ወሳኔ በቱንዚያው ቤን አሊ ላይ ከተወሰደው ውሳኔ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ብቻ ሳይሆን ማንኛውም አምባገነን ከህዝብ ሰርቆ የሚያጠራቅመው ገንዘብ የስልጣን ዕድሜው ሲያጥር መልሶ አንደማያገኝ ተስፋ የሚሰጥ ነው ተብሎአል።

በተያያዘ ዜና የግብጽ ህዝበ የትግል ውጤት እጣ ፈንታ ምን ሊሆን እንደሚችል የዓለም ህዝብ በጉጉትና በንቃት እየተከታተለው ባለበት በዚህ ወቅት አምባገነኑና ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ኢትዮጵያዊያን በፍጹም ስለ ግብጽ ሁኔታ እንዳያውቁ ለማድረግ የስለላ ስራ እያካሄደ እንደሆነ ዘጋቢያችን ከአዲስ አበባ በላከልን ሪፖርት ገልጹአል::

እንደዘጋቢያችን ሪፖርት በአዲስ አበባ ከተማ በርካታ ሆቴሎች ውስጥ የግብጽን ህዝባዊ አመጽ በአልጃዚራ ቴሌቪዥን ይከታተሉ የነበሩ ኢትዮጵያዊያንን ስሜት በቅርብ የሚከታተሉ ካድሬዎች መመደባቸውንና በአንዳንድ ሆቴሎች ባለቤቶቹ አልጃዚራን አንከፍትም በማለታቸው ከነዋሪዎች ጋር መጋጨታቸው ተሰምቱአል::

ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ በኢትዮጵያ ነጻ ሚዲያ ህዝብ ጆሮ እንዳይደርስ ሌት ከቀን መስራት የጀመረበት ጊዜ ረዘም ያለ ቢሆንም፣ ኢትዮጵያዊያን ግን በተለያዩ የዜና አውታሮች ነጻ መረጃዎችን ለማግኘት እየታገሉ እንደሆነ ተያይዞ የደረሰን ዜና አመልክቱዋል::

# ማስታወቂያ

## ለአራተኛ ጊዜ ተቋዋርጦ የነበረው የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ስርጭት በ24 ሰአት ውስጥ አገልግሎት መስጠቱን ቀጠለ

የካቲት 2፣ 2003 ዓም በኢትዮጵያ ሰዓት አቆጣጠር ከጠዋቱ 5:45 ላይ ወደ ኢትዮጵያና አካባቢ ሀገራት የሚያስተላልፈው የቀጥታ ፕሮግራም ስርጭት ለአራተኛ ጊዜ እንደገና መታወኩን አስታወቆ የነበረው የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ኢሳት ያጋጠመውን ፈታኝ ችግር ተቋዋቁሞ ስርጪቱን እንደገና የጀመረ መሆኑን አስታወቀ።

ኢሳት ቀደም ብሎ ይሰጥ የነበረው አገልግሎት በተቋረጠበት ወቅት ከሳተላይት ኩባንያው ጋር ተነጋግሮ የሚያገኘውን ውጤት በአስቸኳይ ለህዝብ ይፋ እንደሚያደርግ ገልጾ የነበረ ሲሆን የኢሳት ፕሮግራም የተቋረጠበት ምክንያት ምንም ይሁን ምን ፕሮግራሞቹን በሌላ ሳተላይት፣ በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደ ኢትዮጵያ ለማስተላለፍ ተግቶ እንደሚሠራ ገልጾ ነበር።

አንድ ስማቸው እንዳይገለጽ የፈለጉ የታይ ኮም ኩባንያ ሰራተኛ የኢሳትን ስርጪት መቋረጥ አስመልክቶ መረጃ እንዲሰጡን አቅርበን ለነበረው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ የወያኔ ባለስልጣናት ከሁለት ወር በላይ የኢሳት ስርጭት እንዲቋረጥ ካምፓኒው ላይ ከፍተኛ የሆነ የዲፕሎማቲክ ግፊት ሲያደርጉ እንደነበር ገልጸው በስተመጨረሻው ምን ዓይነት የጥቅም ድርድር አድርገው እንደተሳካላቸው ለማወቅ አልቻልንም ብለዋል። ፤

የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን በትናንትናው እለት ባወጣው መግለጫው ታይኮም የሳታላይት ካምፓኒ ስርጪቱን ከአየር ባወረደ ሃያ አራት ሰአት ባነሰ ጊዜ ውስጥ ኢንተል ሳት በተባለ ሌላ ሳታላይት ካምፓኒ አማካኝነት ወደ አየር መመለሱን ገልጾአል። አዲሱ የሳተላይት ጣቢያ ምንም ተጨማሪ ወጪ ሳያስፈልግ ትንሽ ብቻ የሳተላይት መቀበያ ሳህኑን በማዞር ማግኘት እንደሚቻል እና በዚህ በአዲሱ ኢንቴል ቻናል አልጄዚራን የመሳሰሉ ትላልቅ የተሌቪዝን ጣቢያዎችን ማግኘት እንደሚቻል ለማወቅ ተችሎአል። አዲሱን የኢሳት ፍሪኩዌንሲ ለማወቅ ለምትሹ አድማጮቻችን ፤

Intelsat 10 at 68.5 East
C-band
Transponder 14
Downlink: 3808 V
Symbol rate: 10340
FEC: ¾

መሆኑን እንገልጻለን::

በቱኒዚያ ተቀጣጥሎ ግብጽንና ሌሎች የሰሜን አፍሪቃ ሃገራትን እያስራደ ያለው የህዝብ አመጽ እንቅልፍ የነሳው የወያኔው ዘረኛና አምባገነን አገዛዝ በቁጥጥሩ ስር በሚገኙት የዜና ማሰራጫ ጣቢያዎች ይህን የህዝብ አመጽ እንዳይተላለፉ ያደረገ ሲሆን ባንጻሩ በነዚህን ሃገራት የተነሳውን የህዝቦች አመጽ የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ኢሳት በስፋት እየዘገበው በመሆኑ ክፍተኛ የሆነ ስጋት ውስጥ እንደከተተው ብዙዎች ይናገራሉ::

የህዝባችንን ነጻና ገለልተኛ መረጃ የማግኘት መብት አፍኖ ዕድሜ ልኩን ለመግዛት ያሰበው ወያኔ ከዚህም በፊት በአረብ ሳት አማካኝነት ይተላለፈ የነበረውን ስርጭት ከካምፓኒው ጋር በመደራደርና ከፍተኛ ገንዘብ በመክፈል እንዳሰናከለው ይታወሳል።

## የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።

**በ 7140፣ 7175፣ 7185 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ እና በ 6100 KHZ በ 49 ሜትር ባንድ**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ፣ ሐሙስ እና ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት እስከ 3፡30፤ እንዲሁም ከምሽቱ 2 ሰዓት እስከ 2፡30 የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org